# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY-SIX: እኔ አልነበርኩም!

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: አቶ ጃለታ AT HOME WITH HIS WIFE**

- ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)
- አቶ ጃለታ (M, 45)

**SCENE 2: ምህረት TELLS ዳንኤል SHE IS PREGNANT**

- ምህረት (F, 15)
- ዳንኤል (M, 16)
- GROUP OF STUDENTS (M/F, 15)

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND THE TWINS MEET ምህረት AT BONGO ACADEMY**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- ቅዱስ (M, 8)
- ብሩክ (M, 8)

- ምህረት (F, 15)

## SCENE 4: አቶ ካሳሁን CALLS ወ/ሮ ለምለም FROM THE AIRPORT ABOUT ቅዱስ AND ብሩክ

- TAXI DRIVER (M, 30)
- አቶ ካሳሁን (M, 50)
- ወ/ሮ ለምለም (F, 40)

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የሚቀርብላችሁ ተከታታይ ድራማ ነዉ። በዚህ ድራማ ስለ ሶስት ወጣቶች እና ቤተሰቦቻቸው ስናደምጥ ቆይተናል። እስቲ የሬዲዮ ድራማው የመጀመሪያው ዙር ከመቋጨቱ በፊት እስካሁን የሆኑትን መለስ ብለን እንመልከት።

የምህረት የወር አበባ ባለመምጣቱ ጓደኛዋ ትዕግስት ዶክተር ዘሪሁንን ጠርታ ሐኪሙ ከምርመራው በኋላ አስደንጋጭ ዜና ነግረዋታል።:

2. **DR. ZITO (EP 25, 44):** "ምህረት እስቲ ተቀመጭ። ምርመራውን አጠናቅቄያለሁ። ውጤቱ የሚያሳየው ...ነፍሰ ጡር መሆንሽን ነው።
3. ምህረት : "ወይኔ ጉዴ። ሞት ይሻለኛል።!" (+ 56) "እኔ አላምንም እርጉዝ ነኝ ማለት ነው? ። በውስጤ የዳንኤል ልጅን ተሸክሜያለሁ ... ..."

ብቻ ምህረት ለዳንኤል ማርገዟን ስትነግረው ምን ይል ይሆን? ይህ በእንዲህ እንዳለ ምህረት የማታውቀው ሌላም ነገር አለ።ብሩክ እና ቅዱስ ወደ ቤተሰቡ ተመልሰው መጥተዋል! እንደማለመታደል ሆኖ ግን አባትየው አቶ ሙላቱ የአቶ ጃለታን ንብረት ዘርፈሀል ተብለው በቁጥጥር ስር ውለዋል።

በማግስቱም ጠዋት ወ/ሮ ሉሊት እና መንታ ልጆቻቸው ይህንን ለምህረት ለመንገር ወደ ትምህርት ቤቷ

ሲሄዱ የዳንኤልን አባት አቶ ካሳሁንን በአጋጣሚ መንገድ ላይ አግኝተዋቸዋል። :

4. አቶ ካሳሁን (EP 25, 101): "ምን? እናንተ እዚህ ምን ታደርጋላችሁ?"

5. ብሩክ : "እማዬ! እንዲሄድ ንገሪው። እባክሽ ሊወስደን እንደማይችል ንገሪው። "

6. ወ/ሮ ሉሊት: "ይቅርታ ያድርጉልኝ እና ልጆቼ እርስዎን የፈሩ ይመስላል። ምክንያቱን ሊነግሩኝ ይችላሉ?"

አቶ ካሳሁን ምክንያት ፈጥረው አምልጠዋል። የደበቁት ምስጥር ምን ይሆን? ምህረትንስ ያገኟታል ?በህይወቷ እየተከሰተ ያለውን ችግር እንዴት ትቋቋመዋለች? በዛሬው « እኔ አይደለሁም» በተሰኘው የጭውውት ክፍል እንደርስበታለን። በመጀመሪያ ግን ወደ አቶ ጃለታ ቤት ጎራ ብለን የሚሆነውን እናድምጥ።.አቶ ጃለታ እና ባለቤታቸው ምሳ እየበሉ ነው። …

## SCENE 1: አቶ ጃለታ WITH WIFE AT HOME IN THE MORNING

7. **DAYTIME ATMO**

8. **SFX: CUTLERY, ወ/ሮ ዘውዲቱ EATING**

9. **SFX: አቶ ጃለታ TURNS THE PAGES OF HIS NEWSPAPER**

10. ወ/ሮ ዘውዲቱ : እስቲ ስለሰማኸው ዜና ንገረኝ። ሊገሉኝ የነበሩትን ሌቦች ያዙዋቸው?

11. አቶ ጃለታ: አይ የንጉሴ እናት ይህን ያህል አታጋኚ። ያን ያህል አስጊ ሁኔታ አልነበረም።

12. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (grumbling) እእእ… እንደዛ ስትል ነገሩ ለእኔ ምን ያህል መጥፎ እንደነበር የምታውቅ ይመስል!

13. **SFX: NEWSPAPER FOLDED AND PLACED ON TABLE**

**14.** አቶ ጃለታ: (curious) ታውቂያለሽ! የንጉሴ እናት የልጃችንን የፀባይ መለወጥ ምክንያት ልረዳ አልቻልኩም። ንጉሴ መጥፎ ልጅ እየሆነ ነው። ማጤስ ጀምሯል። ከኛ ጋ አይስማማም። በጥባጭ ሆኗል። በዛ ላይ - መኪናችንን እስከመስረቅ ደርሷል። ግን እስካሁን የክፍል አለቃ ነው። በባዮሎጂ ፈተናም ከክፍል ከፍተኛውን ውጤት ያገኘው እሱ ነው። ጨርሶ እኮ የማይጣጣም ነገር ነው።

**15.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ያው ሰዎች ጉሩምስና የሚሉት ነዋ! እርሱ ማን እንደሆነ ወይንም ማንን ለመሆን እንደሚፈልግ ማወቅ አዳግቶታል። ሁለት ገፅታዎችን መላበስ ጀምሯል። በአንድ በኩል አይታዘዝም፣ ኃላፊነት አይሰማውም እንዲሁም ግዴለሽ ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ ትምህርቱን በትኩረት የሚከታተል ይመስላል። ቢያንስ ይህ አንድ ነገር ነው። …

**KW BEGIN**

**16.** አቶ ጃለታ: ግን እንደው አንድ ሰው ህጎችን መጣስ ሲጀምር ትምህርቱንም ችላ ይላል አይደለም እንዴ?

**17.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እኔንጃ… ምን አልባት አንድ ሰው ሊማርክ ፈልጎ ይሆናላ?

**18.** አቶ ጃለታ: አ! … ይህን በጭራሽ አላሰብኩትም።

**19.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ይህ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እራሱም የሆነውን በውል የሚያውቅ አይመስለኝም። ….

**20.** አቶ ጃለታ: እንደሚመስለኝ አንቺ ንጉሴን አበላሽተሽዋል። አሁንም እየተበላሸ ነው ያለው።

**21.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : እንዴት እንዲህ ብለህ ትወቅሰኛለህ? --

**KW END**

**22. SFX: MOBILE PHONE RINGING**

**23.** አቶ ጃለታ: ቆይኝማ ይህንን ጥሪ መመለስ አለብኝ **(answers phone in bad tone)** አቶ ጃለታ ነኝ - ማን ልበል? ማን? ... ኦ መርማሪ ! ይቅርታ አድርግልኝ እንደምን አለህ... **(pause)** ጥቂት መረጃዎች? እሺ ቀጥል።**(pause).** እውነትህን ነው? መቼ? ትናንትና ማታ? በጣም ጥሩ። ባለቤቴ እና እኔ አሁኑኑ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እናመራለን።

**24. SFX: MOBILE PHONE CALL ENDED**

**25.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(excited)** ብቻ ሙላቱን አሰሩት እንዳትለኝ።

**26.** አቶ ጃለታ: **(fondly)** እያልኩሽ ነው። ሙላቱን አስረውታል።

**27.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : አየህ!

**28. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE TWO: ምህረት TELLS ዳንኤል SHE IS PREGNANT</u>**

**29. SFX: INTERIOR CLASSROOM ATMO, BREAK TIME, STUDENT MURMURS**

**30.** ምህረት : **(whisper)** ዳንኤል ይህ ትክክለኛ ጊዜና ቦታ እንዳልሆነ አውቃለሁ።--

**31.** ዳንኤል : **(still angry)** ምህረት እባክሽ በማንኛውም ደቂቃ አስተማሪ ሊገባ ይችላል። በኋላ--

**32.** ምህረት : ዳንኤል እኔ ከእዚህ በላይ መታገስ አልችልም። ላናግርህ በፈለኩ ጊዜ ሁሉ ልትሸሸ አትችልም።

**33.** ዳንኤል : **(cuts her short)** ምህረት እኔ --

**34.** ምህረት : ልነግርህ የምፈልገውን አስጨርሰኝ እባክህ!

**35.** ዳንኤል : እሺ እሺ ቀጥይ እሰማሻለሁ።

**36.** ምህረት : አባትህን እንደገና ማነጋገር አለብህ, ቦንጎ አካዳሚን ለቀህ ላቦሪያ ልትሄድ አትችልም።

**37.** ዳንኤል : **(laughs)** እና በትክክል ምን ብዬ እንድነግረው ነው የምትፈልጊው?

**38.** ምህረት : **(softly)** ዳንኤል አርግዣያለሁ።

**39.** ዳንኤል: **(disbelief)** እስቲ ድገሚው ምንድን ነው ያልሽው?

**40.** ምህረት : አርግዣያለሁ ነው ያልኩህ ዳንኤል ።

**41.** ዳንኤል: **(insensitive)** እሺ ሰማሁሽ። እና ለምንድን ነው ይህን እየነገርሽኝ ያለሽው?

**42.** ምህረት: **(shocked)** ለምን? ተጠያቂው አንተ ነሃ። የህፃኑ አባት ነህ። ወላጆች ልንሆን ነው።

**43.** ዳንኤል: **(defensive)** ማን ? እኔ? በፍፁም! መቼ?እና እንዴት? ኃላፊነት የለብኝም። በዛ ላይ አባት ለመሆን ዝግጁ አይደለሁም። ሌላ የምታሞኚው ፈልጊ።

**44.** ምህረት : **(almost in tears)** እንዲህ ልትልማ አትችልም ዳንኤል። ኋላፊነትህን ልትክድ አትችልም። አንተ ነበርክ ላንተ የነበረኝን ፍቅር እንዳሳይህ የፈለከው።

**45.** ዳንኤል : አይደለም። እኔ ጓደኛሽ ብቻ ነው የነበርኩት። **(dismissing her)** ይቅርታ አድርጊልኝ ምህረት ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ራሴን ማዘጋጀት አለብኝ።

**KW BEGIN**

**46. SFX: PAGES OF A BOOK BEING OPENED**

**47.** ምህረት : **(total disbelief, loudly)** ዳንኤል እያደረከኝ ያለውን በፍፁም ማመን አልችልም።

**48. SFX: CLASS REACTS WITH MURMURS AND WHISPERS**

**49.** ዳንኤል: **(to the class)** ምን ታፈጣላችሁ? ከምትሰሩ ሌላ ስራ የላችሁም። ወይንስ ሁለት ሰዎች ሲወያዩ አይታችሁ አታውቁም።

**50.** ምህረት: **(crying uncontrollably)** ዳንኤል በሙሉ ልቤ አምኜህ ነበር። እና ይሄ ነው መልስህ?

**51.** ዳንኤል : **(trying hard to control the situation)** ምህረት። ምንም አይደል። ከባድ እንደሆነ ይገባኛል። ግን እንደምንም ብለሽ ትወጪዋለሽ። አሁን ግን ይቅርታ አድርጊልኝ በእውነት ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ መዘጋጀት አለብኝ።

**KW END**

ምህረት : **(breaks down in tears)**

**52. SFX:** ምህረት **'S FOOTSTEPS RUNNING AWAY**

**53. SFX: DOOR OPENED AND CLOSED**

**54.** ዳንኤል : ምህረት - የት ነው የምትሄጂው?

**55. SFX: CLASS REACTS WITH SUSPICION AND MURMURS**

**56.** ዳንኤል: (to class) ምን ታንሾካሽካላችሁ! ምህረት ከባድ ችግር ላይ ናት ። እኔ ደግሞ ልረዳት እየሞከርኩ ነው። ይሄው ነው፤ ምን እዚህ።

**57. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND THE TWINS MEET ምህረት AT BONGO ACADEMY**

**58. AMBIENCE SCHOOL CORRIDOR**

**59.** ወ/ሮ ሉሊት: በሉ ልጆች ይህ ትምህርት ቤት ጥብቅ ህጎች አሉት። ማንንም ልንረብሽ አይገባም። (short pause) የእህታቹህ ክፍል ምኑጋ እንደሆነ አላውቅም።

**60.** ብሩክ : እማ ተመልከች። ያቻትልሽ!

**61.** ወ/ሮ ሉሊት: እእ?

**62.** ምህረት : (crying outside door)

**63.** ቅዱስ : (excited about seeing ምህረት ) ምህረት ! መጥተናል።

**64. SFX: FOOTSTEPS RUNNING**

**65.** ምህረት: (tries to cover tears) ቅዱስ ? (excited too) ብሩክ ! - እማዬ! እዚህ ምን ታደርጋላችሁ? አያቶቼ ቤት ያላችሁ መስሎኝ ነበር። እኔ አላምንም።

**66.** ወ/ሮ ሉሊት: (concerned) ምህረት፤ ምን ሆነሽ ነው? ክፍል ውስጥ መሆን አልነበረብሽም? ለምንድን ነው የምታለቅሽው? ንገሪኝ ልጄ ምን ሆነሻል?

**67.** ምህረት: (weak but adamant) ምንም... ደህና ነኝ። በእውነት...

**68.** ወ/ሮ ሉሊት: አይዞሽ ልጄ። አንድ መጥፎ ዜና አለ። ስለ አባትሽ ነው። ...

**69. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 4: አቶ ካሳሁን CALLS ወ/ሮ ለምለም FROM THE AIRPORT ABOUT ቅዱስ AND ብሩክ**

**70. TRAFFIC ATMO**

**71. SFX: CAR BOOT BEING CLOSED**

**72. TAXI DRIVER:** ሻንጣዎ ይሄው ጌታዬ። ወደ ሀገርዎ መልካም በረራ ይሁንልዎ።

**73.** አቶ ካሳሁን **:** በፍጥነት አየር ማረፊያ ስላደረስከኝ አመሰግናለሁ ሹፌር። ይኼው እዚህ በቆየሁበት ጊዜ ለሰጠኸኝ አገልግሎት። እንካ - ይሄ ደግሞ ላንተ ነው።...

**74. SFX: BANK NOTES BEING COUNTED AND HANDED OVER**

**75. TAXI DRIVER: (excited)** አመሰግናለሁ አቶ ካሳሁን። በጣም ደግ ሰው ነዎት።ደህና ይሁኑ።

**76. CAR DOOR OPENED, CAR ENGINE STARTED, CAR DRIVES OFF**

**77.** አቶ ካሳሁን: **(Thinking aloud)** ዛሬ በረራ በማግኘቴ ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን። እነዚያ ልጆች የሚገርሙ ናቸው። እንዴት ይሆን እዚህ ሊመጡ የቻሉት። ማንስ ይሆን የተባበራቸው? እዚህ ለባለስልጣኖች ስለኔ ማንነት ቢናገሩብኝ ። ወይጉድ የለም... በተቻለኝ ፍጥነት ወደ ቤቴ መብረር አለብኝ።

**78. SFX: FOOTSTEPS -** አቶ ካሳሁን **WALKS INTO AIRPORT HALL**

**79. SFX: ELECTRIC DOOR OPENS AND CLOSES**

**80. SFX: SUITCASE BEING ROLLED ALONG THE FLOOR**

**81. AIRPORT ATMO WITH ANNOUNCEMENTS ETC.**

**82.** አቶ ካሳሁን : **(thinking furiously)** ለምለምን ማመን አልነበረብኝም። ድሮም ስራንና ደስታን መቀላቀል አይገባም። ምን እንደተከሰተ መመልከት ነው። ይኸው መመልከት ነው የሆነውን። እንድታውቀውማ ማድረግ አለብኝ።

**83. SFX: NUMBERS ON MOBILE PHONE BEING DIALLED**

**84. SFX: CALLING TONE**

**85.** አቶ ካሳሁን : ስልኩን አንሺ አንቺ ደደብ ሴትዮ… **(short pause)** ለምለም! ለምለም? ትሰሚኛለሽ? … … ደንቆሮነሽ እንዴ? …የወንድምሽን ልጆች አየኋቸው ነው የምልሽ። ትናንት! እዚህ ኪሲምባ ነው ያሉት። ከእናታቸው ጋ። ምን እየተከሰተ እንዳለ ልትነግሪኝ ትችያለሽ? … ለምለም? ለምለም!

**86. SFX: PHONE CALL DISCONNECTED**

**87.** አቶ ካሳሁን : የማትረባ!

**88. SFX: AIRPORT ANNOUNCEMENT OF FLIGHT DELAY TO LABORIA**

**89. VOICE:** "በቴክኒክ ብልሽት ምክንያት የበረራ ቁጥር 305 የላቦሪያ በረራ ለ45 ደቂቃ ያህል ይዘገያል። መንገደኞቻችንን ለደረሰው መጉላላት ይቅርታ እንጠይቃለን።"

**90.** አቶ ካሳሁን : ፈጣሪ እንደው ምን በድዬህ ነው ይህንን ያዘዝክብኝ።

**91. MUSIC INTERLUDE**

## 92. OUTRO - NARRATOR:

ወደ ሀገራቸው ለመመለስ አቶ ካሳሁን አይኖፕላን ሊገቡ በዝግጅት ላይ ሳሉ እኛም «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተኘውን የመጀመሪያ ዙር ድራማ 25ኛና የመጨረሻ ክፍል እናጠናቅቃለን። የዚሁ ጭውውት ሁለተኛው ዙር «ከባድ ውጤቶችን መጋፈጥ» የሚል ርዕስ ይዟል። ታሪኩ ገና መጀመሩ ነው። ምህረት እርግዝናውን ትገፋበት ይሆን ወይንስ ፅንሱን ታስወርዳለች? አቶ ካሳሁንስ በሕገ ወጥ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ወንጀል ተጠያቂ ይደረጉ ይሆን? የአቶ ሙላቱስ ጉዳይ? የዘረፋው ክስ ውድቅ ይደረጋል? ወይንስ ወህኒ ይወርዳሉ? ንጉሴ ዳንኤል ፣ ትዕግስት እና መንታ ወንድማማቾቹ ቅዱስ እና ብሩክስ ? ይህ ሁሉ በሁለተኛው አጋማሽ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«ከባድ ውጤቶችን መጋፈጥ» በሚል ይጠብቃችኋል። የዚህ ድራማ ደራሲ ክሪስፒን ሙዋኪዴዎ ነው።

ያለፉትን 26 ክፍሎች ደግመው ለመስማት ከፈለጉ ድረ ገፃችን dw.de/lbe ነው። ዳንኤል ስለ ምህረት ዕርግዝና ምን እንደሚያስብ ለማወቅ ደግሞ ላቦሪያ ላሉ ጓደኞቹ በሚስጥር የሚቀርፀውን የቪዲዮ ዘገባውን ተከታተሉ። ፌስቡክ ላይም ልትከታተሉን ትችላላችሁ። ስላዳመጣችሁን እናመሰግናለን። እስከሚቀጥለው ጊዜ ደህና ሁኑ።